ከሰፈር ሰፈር እየዞሩ ይህን ሥራ ይሠሩ በነበረበት ጊዜ ሁሉ "ይደክመዋል ብለህ ለእኔ እንዳታስብ አስፈላጊ በሚመስል ቦታ ሁሉ እየወሰድከኝ ችግሩን መቋቋም አለብን" በማለት አባቴ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡ ለዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ በሚለማራበት ቦታ ሁሉ "ጳውሎስ" በተባለ ስም ይጠቀም ነበር፡፡ ለዚህ ሐዋርያዊ አገልግሎታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ "ጳውሎስ" የተባለ ስሙን ለመጀመሪያ ወንድ ልጁ መጠሪያነት ሰጥቶታል፡፡



# ምዕራፍ ፬

## ዘርፈ ብዙ የአገልግሎት ዘመናት
## ፲፱፻፶ - ፲፱፻፷፭

# የሊቃውንት ጉባኤ -ጠባቧ የአባቴ መንገድ

የቅዱስ ማርቆስ መንበር ከሚገኝባት ከግብጽ እየተሾሙ ይመጡ የነበሩ ግብጻውያን ጳጳሳት በኢትዮጵያውያን እንዲተኩ ከተደረገ በኋላ በተቋቋመው የጠቅላይ ቤተ ክህነት መዋቅር ወስጥ የተቋቋመው የሊቃውንት ጉባዔ ቀደም ብሎ ከ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ጀምሮ መንፈሳዊ ጉባኤ እየተባለ ይጠራ የነበረውን ከፍተኛ መዋቅር እንዲተካ የተደረገ ነው፡፡

ይህ የተፈጸመው በመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዘመነ ክህነት ሲሆን የጉባኤው መቋቋም የንጉሠ ነገሥቱን ይሁንታ ያገኘ ነበር፡፡ የሊቃውንት ጉባኤው ዋነኛ ዓላማ የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖና መጠበቅ ሲሆን ዘርዘር ተደርጎ ሲታይ የጉባኤው ዓበይት ተግባራት ከዚህ በታች በሰፈሩት ጉዳዮች ላይ በይበልጥ የሚያተኩር ነበረ፡፡

፩/ መጻሕፍትን ከግዕዝ ወደ አማርኛ መተርጐም፡፡


፪/ በሃይማኖት ዙሪያ ለሚነሡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት፡፡

፫/የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖና ተንተርሶ በተቅዋምም ሆነ በቡድን ወይም በግለሰብ ደረጃየሚዘጋጁ መንፈሳውያን መጻሕፍትን መመርመር፣ ማረም፣ መፍቀድ ወይም ማገድ፡፡

፬/የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የሚጋፉ ግላዊም ሆነ ቡድናዊ እንቅስቃሴዎችን በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት መከላከል ናቸው፡፡

የሊቃውንት ጉባኤው በተቋቋመ ጊዜ በሰብሳቢነት እንዲመሩ ከተሾሙ ሊቃውንት የመጀመሪያው ክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ሲሆኑ ክቡር ንቡረ እድ መኩሪያ አብየሆይና ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ





አባቱ የሊቃውንት ጉባኤውን ከመቀላቀሉ በፊት የተፈተነውን ፈተናና የሰጠውን መልስና ያገኘውን ውጤት የሚያሳይ ቃለ ጉባኤ

(በፊት ሊቀ ሊቃውንት ተሰፋ) ከ፲፱፻፵፫ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፶፬ዓ.ም በነበሩት ፲ ዓመታት በቅደም ተከተል ተሹመዋል፡፡ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ በምትካቸው በሰብሳቢነት የተሾመው አባቴ ነው፡፡

አባቴ በቤተ ክህነት ሠራተኛነት የተቀጠረው በ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም ሲሆን ለሰብከት ክፍል ከተመደበ በኋላ ደመወዝ እየተከፈለው የሊቃውንት ጉባኤ አባል ሆነ፡፡ የተሰጠው ሥራም ቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ ባስልዮስ በሰጡት ትእዛዝ መሠረት በጊዜው ከነበሩ አበው ሊቃውንት መምህራን ብሉይን እንዲያስቀር ነበር፡፡

ፓትሪያርኩ ትእዛዝ ቢሰጡም በቅድሚያ ተገቢውን ፈተና መፈተን ነበረበት፡፡ በዚሁ መሠረት በሊቃውንት ጉባኤ የቀረበለትን ፈተና ወስዶ ተገቢውን ውጤት በማግኘቱ በችሎታው ታምኖበት ቅጥሩ ተከናወነ፡፡

አባቴ በሊቃውንት ጉባዔ አባልነትና ሰብሳቢነት ዘመኑ የፈጸማቸው ተግባራት እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ የሊቃውንት ጉባኤውን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መሥዋዕትነት እየከፈለ የመሪነት ሚናን ተጫውቷል፡፡ የቤተ ክህነቱ ድጋፍ ያስኬደውን ያህል በሰላም፥ ድጋፍና ትብብር ባጣባቸው ጉዳዮች ላይ ደግሞ ግላዊ ኃላፊነትን በመውሰድ ሠርቶ ለማሠራት በመጣጣር ለ፴፩ ዓመታት አገልግሏል፡፡ በጉባኤው ውስጥ አብረውት ያገለግሉ ከነበሩ የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመተባበር ያበረከታቸው ግበይት ተግባራት ሲተነተኑ እጅግ ብዙ ሲሆኑ በተለይ የትርጉም ሥራዎቹ ሳይታወሱ መታለፍ የለባቸውም፡፡

## የትርጉም ሥራዎች

በአባቴ ሰብሳቢነት ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ዋነኛ ሥራዎች አንዱ በግዕዝ የተጻፉ የሃይማኖት መጻሕፍትን ወደ አማርኛ ቋንቋ መተርጐም ነበረ፡፡

ከዓለም አብያተ ክርቲያናት እጅግ ቀደምት የሆነችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት፥ ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል



ባደረገችው መንፈሳዊ እርምጃ የሚቀድማት እንደ ሌለ ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ይህ ቀደምትነቷና ጥንታዊነቷ ከመጽሐፈ ሄኖክ እስከ መጻሕፍተ ሊቃውንት ለተቀበለቻቸው ቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛነት በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሃይማኖታዊ ነን የሚሉ ክፍሎች ይህንን ግልጽ እውነት በመካድ ክደውም ለማስካድ ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምርበትን መጽሐፍ ቅዱስ አጣርሰውና አዛብተው ተርጉመውታል፡፡ እልፈው ተርፈውም ለእነሱ የቅሰጣ ተግባር የማያመቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ሙሉ ለሙሉ እንዲወጡ አድርገዋል፡፡

በዚህ መልክ እንዲታተምና በየሰው እጅ እንዲገባ በተደረገው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፈጸሙትን መሰሪ የቅሰጣ ሥራዎች የማያውቀው ምእመን የተጻፈው ትክክል እየመሰለው ራሳቸው ተርጓሚዎች በቆፈሩለት የክሕደት መንገድ በመሄድ ከእናት ቤተ ክርስቲያን እየተነጠለ ቀርቷል፡፡ ይህንን በትርጉም ምክንያት የተፈጠረ ችግር ለመቋቋምና ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን ተጨማሪ ጉዳት ለማስቀም ይቻል ዘንድ በአባቴ ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ ዋነኛ ሥራ አድርጎ ከያዛቸው ተግባራት አንዱ የሃይማኖት መጻሕፍትን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ቋንቋ መተርጎም ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ጉባኤው ከሠራቸው የትርጉም ሥራዎች ዋነኛና ተጠቃሽ የሆኑት ሥራዎች፥ ፩ኛ፤ ሐዲስ ኪዳን ፪ኛ፤ ሃይማኖተ አበው ፫ኛ፤ መጽሐፈ ግጻዌ ፬ኛ፤ ግብረ ሕማማት ፭ኛ፤ ድርሳነ ሚካኤልና ፮ኛ፤ መጽሐፈ ተክሊል ዋንኞቹ ናቸው፡፡

## ሐዲስ ኪዳን

አባቴና የሊቃውንት ጉባኤው አባላት የሐዲስ ኪዳንን የትርጉም ሥራ መቼ እንደ ጀመሩት ማስረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ሥራው እልቆ ለኅትመት የበቃው ግን በብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን ነው፡፡ ሕዝብ በሐሰተኛ ትርጉም እንዳይታለልና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናም እየተበረዘ እንዳይሄድ በማሰብ ሐዲስ ኪዳንን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የመተርጎም ሥራ አባቴ በጥብቅ ከታገለላቸው ሥራዎች አንዱ ነበር፡፡ ይህ የትርጉም ሥራ ሲከናወን የጽሕፈት መሣሪያዎችንና በቂ የሰው ኃይል ምደባን ለማግኘት

በተደጋጋሚ ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ መልስ በማጣቱ የጐደለውን በየግል ጥረታቸው እያሟሉ ግባቸውን አሳክተዋል፡፡

በተቋም ደረጃ ቤተ ክህነቱ ቅድሚያ ሰጥቶ፣ ቅንጅት ፈጥሮ ሊሠራው ይገባ የነበረውን ይህንን ከፍተኛ ሥራ፤ በዕድሜ፣ በጤናና በገንዘብ ሀቅም የተዳከመ ሁኔታ ውስጥ የነበረው አባቴ ኃላፊነት ወስዶ ሲሠራና ሲያሠራ ብዙ ችግር ከዚያው ከቤተ ክህነቱ ደርሶበታል፡፡ ከጉባዔው አባላት መካከል አንዳንዶቹን አግኝቼ እንደተረዳሁት ከድጋፍ ይልቅ እንቅፋት የበዛበት የሐዲስ ኪዳን ትርጉም ሥራ ሊሳካ የቻለው አብዛኛው ሸክም በአባቴ ትከሻ ላይ አርፎ ነበር፡፡ ሆኖም ግን መጽሐፉ ስንትመት በቅቶ ገበያ ላይ ከወጣ በኋላ በመጽሐፉ መቅድም ላይ አባቴ በሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነቱ በሰጠው መግለጫ ግርጌ የተጻፈው ስሙ በነጭ ቀለም እየጠፋ እንዲሸጥ ተደርጓል፡፡

## <u>ሃይማኖተ አበው</u>

አባቴ የሃይማኖተ አበው ትርጉም እንዲሠራ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ሠርቶ የማሠራት ፍላጎት ነበረው፡፡ ምክንያቱም ሃይማኖተ አበው ከተተረጐመ ቀጣዩ ትውልድ እንብቦ በሚረዳው ቋንቋ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ታሪክ ለማወቅ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በሌሎች መካከል ያለውን ልዩነት ባመጡ ጉዳዮች ላይ ታላላቅ ሊቃውንት የሰጧቸውን ወሳኝ መንፈሳዊ ብያኔዎች ወጣቱ እንዲያውቅ ለማድረግ ከፍተኛ ጉጉት ነበረው፡፡ በመሆኑም በትርጉም ሥራው ወቅት ያጋጠሙትን ፈተናዎች ሁሉ በጽና በመቋቋም ይህ ታላቅ መጽሐፍ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለወጣቱ ትውልድ እንዲተላለፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

## <u>መጽሐፈ ግጻዌ</u>

የመጽሐፈ ግጻዌ ትርጕምና ዝግጅት ዋነኛው ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስን በተለይም የሐዲስ ኪዳንን ትምህርት ከዕለታዊ የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ጋር አመጣጥኖና አጣምሮ ለካህናትና ለምእመናን እንዲደርስ ለማድረግ ነው፡፡ ዓበይት ዓላማዎቹም ሁለት ነበሩ፡፡ እነሱም፣



ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ጊዜ የምታከናውነው የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓት ሙሉ መሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ምእመናን እንዲገነዘቡ ማድረግ፣

ለ/ በአብዛኛው በቅዳሴ ትምህርት ላይ ብቻ የተገደበ ዕውቀት ያላቸው ቀዳስያን በየዕለቱ የሚያከናውኑት ክህነታዊ አገልግሎትና ጸሎተ ቅዳሴ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ያለውን መስተጋብር እያስተዋሉ፣ መንፈሳዊ ዕውቀታቸውን እያሰፉ፣ ስብእናቸውን እንዲያንጹበት ለማገዝና ምእመናንንና ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ረገድ ያለባቸውን ኃላፊነት ለማስገንዘብ ነበር፡፡ አባቴ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የተሟላ ትምህርት ለልጆቿ ለማውረስ ከለፋባቸው ሥራዎች የመጽሐፈ ግጻዌ ዝግጅትና ትርጕም አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

## <u>ግብረ ሕማማት</u>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ተሰቅሎ የቤዛነቱን ሥራ እስከ ፈጸመበት እስከ ስለተ ዓርብ ፱ ሰዓት ድረስ ባሉት የሕማማቱ ቀናትና ሰዓታት ውስጥ የሆነውን ሁሉ በዝርዝር የሚተርክ ነው፡፡ ግብረ ሕማማትን በመተርጎም ምእመናን በሚረዱት ቋንቋ የፈጣሪያቸውን የአምላካችን ፍጹም ፍቅር እንዲገነዘቡበት ማድረግ የአባቴ ፍላጎትና ጉጉት ነበረ፡፡

ይህ የትርጕም ሥራ ይሠራ በነበረበት ወቅት ቀን የትርጕም ሥራውን ሲሠራ ውሎ ወደ ቤት ሲመለስ በከፍተኛ ተመስጦና መንፈሳዊ ስሜት ተውጦ ይመጣ ነበር፡፡ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምና ሞት ከባድ የሃዘን ስሜት ያሳድርበት ነበረ፡፡ምን ያህል ልቡ በኀዘን ይሰበር እንደነበረ ጠቅላላ ሁኔታው አሁን ድረስ በዓይነ ኅሊናዬ ይታየኛል፡፡ ከዚህ ግንዛቤው በመነሣትም ቤተ ክርስቲያንና ልጆቿ የጌታን ነገረ መስቀል እንደ ዋዛ እንዳያዩ ብዙ አስተምሯል፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የቀረበላቸውን ልዩ ጥሪ እንዳይዘነጉ ከነበረው ሥጋትና ቁጭት በመነሣትም ብዙ ምክርና ተግሣጽ አስተላልፏል፡፡

ይህም ይታወቅ ዘንድ ዕለተ ስቅለትን በማስመልከት በተለያዩ ዓመታት ስለ ሰቅለት በዓል ለምእመናን ያስተማራቸውን ትምህርቶች ማስታወስ ይበቃል፡፡ በተለይም "የራስ ቅል በሚሉት ሥፍራ"እና "እጅና እግሬን ቸነከሩት" በተሰኙ አርእስት በ ፲፱፻፹፯ እና ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ትምህርቶች በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀል ላይ የነበረውን ስሜት በጉልሕ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አባቱ ከቤተ ክህነት ሥራው ሲታገድ የማብረ ሕማማት ትርጕም ሥራ እልቆ ነበር፡፡

ወደ ሊቃውንት ጉባኤው ትርጓሜ መጻሕፍት ሥራ ስንመለስ አንድ አጽንኦት ሳልሰጠው የማላልፈው ጉዳይ አለ፡፡ ምንም እንኳ መጻሕፍትን የመተርጐም ሥራ ከሊቃውንት ጉባኤው የተግባር ዝርዝሮች አንዱ ነው ቢባልም ጉባኤው የትርጕምን ሥራ እንዲያከናውን የሚያስችለው በቂ ድጋፍ ከቤተ ክህነቱ አይሰጠውም ነበር፡፡ ለአባላቱም ቢሆን በቂ ትኩረት ባለ መስጠቱ የሚከፈላቸው ደመወዝም በጣም ዝቅተኛ ነበረ፡፡

በቢሮ ውስጥ የሚገለገሉበት የጽሕፈት መሣሪያ ለማግኘትም አግባብነት የሌለው ውጣ ውረድ ይገጥማቸው ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ ብዙ ለመሥራት እየቻሉ በጽሕፈት መሣሪያ በሰው ኃይል እጥረትና በቂ ደመወዝ በማጣት ችግር ይሠቃዩ ነበረ፡፡ አባቴ የነበረውን ችግር ተቋቁሞ ዐቅም የፈቀደውን ለመሥራት ይፍጨረጨር ስለ ነበረ ብዙውን ጊዜ በሕመምና በተለያየ ችግር ምክንያት በሥራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት የሚያዳግታቸውን የሥራ ባልደረቦቹን ለማትጋትና ለመርዳት የራሱን ችግር ችሎ የእነርሱን ችግር ለመሸፈን ይታገል ነበር፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ትርጕም በተመለከተም ሐሳቡን ከማመንጨት ጀምሮ ለፍጻሜ እስከ ማብቃት ድረስ ከነበረው ሥራ ከፍተኛው ድርሻ የእርሱ እንደ ነበረ ዐብረውት የሠሩ የጉባኤው አባላት የሚመሰክሩት ሐቅ ነው፡፡

## ድርሳነ ሚካኤል

የድርሳነ ሚካኤል ትርጕም ሥራ ራሱን የቻለ ዓላማ የነበረው ነው፡፡ ይኸውም በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን አንብቦ መረዳት



የማይችለው አዲስ ትውልድ፣አንብቦ በሚገባው ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍት እንዲተረጐሙለት በመጠየቅ ላይ ስለ ነበረ ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ሲባል ነው፡፡ ምእመናንን የሚያሳድዱ አፅራረ ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰ እምነታችንን ለማስካድ ዱር ዳር ሲሉ የምላሰቸው መፍቻ የፈተናቸው መክፈቻ ቍልፍ ከሚያደርጓቸው ተግዳሮቶች መሐል አንዱና ዋነኛው የአዋልድ መጻሕፍት ጉዳይ ነው፡፡

በድርሳነ ሚካኤል መግቢያ ላይ "በጊዜው የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሕዝቡን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ለማሟላት ባይችልም አንዳንድ ተፈላጊ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ወደ አማርኛ ተርጕሞ እንዲታተሙ አድርጓል፡፡ አሁንም ደግሞ በምእመናን ዘንድ ተወዳጅና ተናፋቂ የሆነውን በግዕዝ ብቻ ተጽፎ የነበረውን ድርሳነ ሚካኤል በከፍተኛ ጥንቃቄ ወደ አማርኛ ተርጕሞ እንዲታተም አድርጓል፡፡" በማለት የሰፈረው መግለጫ የሊቃውንት ጉባኤው በጊዜው ከፍተኛ ተፈላጊነት የነበረውን ድርሳነ ሚካኤልን ለመተርጐም ቅድሚያ መስጠቱን ያሳያል፡፡

## መጽሐፈ ተክሊል

ከሰባቱ የቤተክርስቲያንአዕማደ ምሥጢራት አንዱ ስለሆነው ምሥጢረ ተክሊልየሚናገረው የህግና የሥርዓት መጽሐፍ መጽሐፈ ተክሊል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ሴቶችና ወንዶች ልጆቿ በተቀደሰ የጋብቻ ህይወት ክብረው እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን መንፈሳዊ እውቀት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ የመጽሐፉ ትርጉም ቅድሚያ ትሰጥቶት አባቴ ይመራው በነበረውየሊቃውንት ጉባዔ ከግእዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሟል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ስድስት ታላላቅ የሃይማኖት መጻሕፍት የሊቃውንት ጉባኤ አባላትን በማስተባበርና በመምራት የተረጐማቸው ናቸው፡፡ በግሉ ከቢሮ ሰዓት ውጪ ጸሐፊ በመቅጠር የተረጐማቸው መጻሕፍት ደግሞ፣ ሀ) ገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለ) ገድለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሐ) ገድለ ቴዎድሮስ በናድልዮስና መ) ገድለ አርሴማ ናቸው፡፡ እነዚህ በግሉ የተረጐማቸው መጻሕፍት የትርጕም ሥራቸው ካለቀ በኋላ የገንዘብ

ዐቅም ያላቸው ሰዎች አሳትመው ለሕዝብ እንዲያቀርቡ በማበረታታት በመጻሕፍት የማስተማር ዓላማውን በከፊል ከግብ ለማድረስ ሞክሯል፡፡

የቅዱሳንን ስንክሳር በተመለከተ ከግዕዝ ለሚተረጐሙም ሆነ በአዲስ መልክ ስለሚጻፉ መጻሕፍት አባቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርግ ነበረ፡፡ የሚጻፉት ታሪኮች ከግላዊ ስሜት የጸዱና በእውነት ላይ ብቻ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ይፈልግ ነበር፡፡ በተለይም ደግሞ ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ጋር እንዳይጣረሱ የጠመመውን አቅንቶ፣ የጎደለውን በጥንቃቄ አጥንቶና ሞልቶ ለምእመናን መማሪያነት እንዲሆን ማብቃት ዋነኛ የሊቃውንት ጉባኤው ተግባር መሆን አለበት የሚል እምነት ነበረው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ በአባቱ ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባኤ ከነበረው ጽኑ አቋም የተነሣ ከቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ውጪ በግላዊና ቡድናዊ ስሜት አነሣሽነት ይቀርቡ የነበሩ ጽሑፎችን በማገድ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ብቁ አማኝ በሌላቸው አልባሌ መጻሕፍት እንዳይዋጥ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

<u>ለግእዝ ሀልውና ጥብቅና መቆም</u>

አባቱ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እሱ የታየውን ለሌሎች ለማሳየትም ብዙ ደክሟል፡፡ በተለይ ከፍተኛ ትምህርት ተምረናል በሚሉ አንዳንድ ዘመናውያን ልሒቃን አካባቢ ይታይ የነበረው የጋን መብራትነት ሳያንስ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ታሪክና ክብር ለሌላ ለመስጠት የሚታትሩ ሰዎች ሲሠሩት ሁሉ ያዝን ነበረ፡፡

"አባቶቻችሁ ስለአገራችሁ ስለ ኢትዮጵያ ስለ ምንነትና ማንነታችሁ እኔ ዓይኑ ስጨሱ በዳበሳ ያየሁትን ሳላያችሁ" ብሎ እስከ መናገር የደረሰበት ጊዜ ሁሉ ነበረ፡፡

ይህን ስሜቱን ካንጸባረቀባቸው ጉዳዮች መካከል ኢትዮጵያ የሰው ዘር መነሻ ስለ መሆኗ፣ የግዕዝ ቋንቋና ፊደል ባለቤት ስለ መሆኗ፣ ንግሥተ



ሳባ የተባለችው የኢትዮጵያ ንግሥት ንጉሥ ሰሎሞንን ከመጐብኘቷ በፊት እግዚአብሔርን ታውቅ እንደ ነበረ፣ በልበ ሙሉነት ያስተምር ነበር፡፡ በዚህ ረገድ አባቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያነሣቸው የነበሩ የዕውቀቱና የእምነቱ ነጸብራቆች በታሪክ፣ በሃይማኖት፣ በሥነ መንግሥት፣ በአርኪዎሎጂ፣ በሕዝብ አስተዳደር፣ በአስትሮኖሚ፣ በፍልስፍና...ወዘተ ለተሰማሩ ምሁራን እጅግ ጥልቀት ያላቸው የምርምር ሐሳቦችን የሚያጭሩና ፍንጭ ሰጪዎች ናቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት፣ የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ቅርስና ታሪክ የሚመለከቱ ጥያቄዎች በሚነሡበት ጊዜ ሁሉ በመገናኛ ብዙኀንም ሆነ በሌላ መንገድ እንደ አቀራረባቸው መልስ በመስጠት ረገድ የቤተ ክርስቲያኒቱ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱ ነባርና ጥንታዊ ዕውቀት ዋነኛ ተጠያቂ ሰው በመሆን አገልግሏል፡፡

እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል "የግዕዝ ፊደላትና አማርኛ ቋንቋ እያስፈልጉንም እንግሊዘኛ መጠቀም አለብን" ብለው በአንድ ወቅት ተነሥተው የነበሩ ምሁራንን በመድረክ ላይ ተሟግቷል፡፡ በሌላ ጊዜም "የግዕዝ ፊደላት መቀነስ አለባቸው" ብለው የተነሡትንም ተከራክሯል፡፡ ከመላው የአፍሪካ አህጉርና ከብዙ የዓለም አገሮች ኢትዮጵያን ልዩ ከሚያደርጓት ቅርሶች አንዱ የሆነውን የግዕዝን ፊደል እንፈልግም ብለው የሌላ ፊደል ለመጠቀም የመረጡ ኢትዮጵያውያንንም መክሯል፡፡

በሺህ ዓመታት ለሚቆጠር ጊዜ ባልተቋረጠ ቅብብሎሽ በኢትዮጵያ ጸንቶ የኖረውን የዳዊትን ዙፋን በተመለከተም ኢትዮጵያውያን ያለባቸውን ብዥታ አስወግደው በጥራት እንዲየዩ ለማድረግ ጥሯል፡፡ የዘውድን ታሪክና ዕሴት ለመገንዘብ የወጣቱ ትውልድ ፍላጎት ማደግ እንዳለበትና ለዙፋኑ ባዕድነት ሊሰማው የሚገባ ኢትዮጵያዊ መኖር እንደሌለበት ደጋግሞ አስተምሯል፡፡ ነገሥታቱ ከአንድ የተወሰነ ጐሣ የወጡ ካለመሆናቸውም በላይ በቅብዐ መንግሥት የሚሰጣቸውን ጸጋ ተቀብለው ሕዝብን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚቀመጡ ባለ አደራዎች ናቸው፡፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር ዘእም ነገደ ይሁዳ" የሚያሰኛቸውም በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ አድሮ ነግሦ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚመራ የይሁዳ አንበሳ የተባለ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥዩማን

መሆናቸውን ለማመልከት ነው እንጂ አይሁዳውያን ናቸው ለማለት አለመሆኑን ደጋግሞ አስተምሯል፡፡

በተለይም በዐሥራ ዘጠኝ መቶ ስሟኒያዎቹ ውስጥ አዲስ አበባ በሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር በተደረገ የዘውድ መንግሥት ደጋፊዎች ስብሰባ ላይ በመገኘት ስለ ኢትዮጵያ ዘውድና ዙፋን ታሪክ ለስብሰባው ተሳታፊዎች ትምህርት ሰጥቷል፡፡ "ዘውድና ዙፋንን ለኢትዮጵያውያን ልዩ የሚያደርገው ከዓለም መንግሥታት ሁሉ በተለየ ሁኔታ የብዙ ሺ ዘመናት ቅርሳቸው በመሆኑ ነው፡፡ መልካም አስተዳደርንና ብልጽግናን ለማግኘት መፍትሔው የሕዝቡን የባለአገርነት መብትና አካባቢያዊ የአስተዳዳር ሥርዓት ከዘመናዊው ሕይወት ጋር አጣጥሞ ለማራመድ መትጋት እንጂ የዘመናት ታሪክ ያለውን ባለ ታሪክና ባለ ክብር ዘውድ ጥሎ የጨርቅ ክፍያ በማድረግ አይደለም ይል ነበረ፡፡"

## ሐ/ መጻሕፍትን መመርመር፥ ማረም፥ መፍቀድና ማገድ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖና ትንተርሶ በተቋምም ሆነ በቡድን ወይም በግለሰብ ደረጃ የሚጻፉ ወይም የሚተረጎሙ መጻሕፍትንና የተለያዩ ጽሑፎችን ወደ ኅትመት ከመሄዳቸው በፊት መመርመር፥ ማረም፥ መፍቀድ ወይም ማገድ የሊቃውንት ጉባኤው ሥራ ነበረ፡፡ አዳዲስ መጻሕፍትን በመድረስም ሆነ የትርጉም ሥራን በመሥራት ወደ ጉባኤው ሥራቸውን ከሚያቀርቡ ሰዎች መካከል ቅን ልብና እውነተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት የመስጠት ዓላማ የነበራቸው ሰዎች የመኖራቸውን ያህል ሃይማኖትን የመበረዝና የመከለስ ድብቅ ዓላማ የነበራቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ባለማወቅ የሚሳሳቱም ነበሩ፡፡

ከነዚህ መሐል ስሕተታቸው ሲነገራቸው እርምት ለመውሰድ ፈቃደኞች የነበሩ ሲሆን መታረም የማይፈልጉም ይገኙባቸው ነበር፡፡ ከግለሰቦች ውጪ በተቋም ደረጃ በቤተ ክህነቱ የሚዘጋጁ ሃይማኖታዊ ጽሑፎች፣ ቢጋዜጣና በመጽሔት የሚታተሙ የኅትመት ውጤቶችም በጉባኤው የሚመረመሩበት ጊዜ ነበረ፡፡ በዚህ ረገድ አባቴና የጉባኤው አባላት ሰፊ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ መጻሕፍትን አዘጋጅተው ጉባኤው ካገደባቸው



ግለሰቦች መካከል አንዳንዶቹ በሥራቸው ላይ የተጣለውን እገዳ ቀጥታ ከአባቴ ጋር በማዛመድ ከጉባኤው የሥራ ጠባይ የተነሣ እንደታገደባቸው ከመቀበል ይልቅ ግላዊ ምክንያት እየሰጡ አባቴን መውቀስና ማማረር ይቀናቸው እንደ ነበር በተለያዩ ጽሑፎች ላይ አንብቤአለሁ፡፡

አባቴ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ለሚነሣ ማንኛውም አንኳል ነገር ድርድር የማያውቅ ጥብቅ አቋም ነበረው፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ ፈተናዎችን አስተናግዷል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከነበሩ ሰዎችም ጋር ብዙ ትግል አድርጓል፡፡ ከነዚህ መካከል በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከምታምነውና ከምታስተምረው ውጪ የሆነ እምነት በማፍለቅ የጻፉትን ጽሑፍ ያገደባቸው ግለሰቦች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ቅሬታ ያሳደሩ ከዚያም አልፈው አባቴንና የሊቃውንት ጉባኤውን በመዝለፍ የሚታወቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከነዚህ ሰዎች መካከል ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ፣ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስና አቶ ዓለማየሁ ሞገስ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ቄስ አስትርአየ ጽጌ የሚባሉ በሀገረ አሜሪካ ኗሪ የሆኑ ሰው ደግሞ በዚሁ በእመቤታችን ጉዳይ የተነሣ በአባቴላይ የዘለፋ ብዕራቸውን ካነጣጠሩ ሰዎች አንዱ ናቸው፡፡

## ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ በዐሥራ ዘጠኝ ስድሳዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ነበሩ፡፡ በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ከዓመታት እስር በኋላ ተፈተዋል፡፡ከእስር ቤት እንደተፈቱ እመቤታችንን ድንግል ማርያምንና አገራችንን ኢትዮጵያን በተመለከተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከምታምነውና ከምታስምነውየተለየ ትምህርት የያዘመጽሐፍ ጽፈው የሊቃውንት ጉባኤ እንዲመረምረው አቀረቡ፡፡በመጽሐፉ ላይ ጠቅላላ ጉባዔው ከመከረበት በኋላ ጉዳዩን ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና አንጻር ለማየትና ለማቃናት የውይይት ዕድል ሠጣቸው፡፡ ሆኖም ግን የቀረበላቸውን ዕድል ባለመጠቀም የራሳቸውን መንገድ ይዘው አዲስ

ትምሕርት ማራመድ ጀመሩ፡፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ የመሰላቸውን መንገድ የመከተል የግል መብታቸው የተጠበቀ ቢሆንም አባቴና የሊቃውንት ጉባኤው ግን የእሳቸውን አዲስ ትምህርት ሊቀበልና ቡራኬ ሊሰጥ የሚችልበት ምንም ሁኔታ አልነበረም፡፡የአካሄዳቸው ነገር ያሳዘነው አባቴ በትህትናና በወንድማዊ መንፈስ ምክር ሊሰጣቸው ሞክሮ የነበረ ቢሆንም የሰጡት አጸፋታ መልስ ግን ለወሬም የማይመች ነበረ፡፡ ይኸው መልሳቸው "ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ" በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ይገኛል፡፡

<u>መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ</u>

"ተሐድሶ" በሚባል ዘመን አመጣሽ እምነት አራማጅነቱ የሚታወቀው መምህር ጽጌ ስጦታው የተባለ የመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ተማሪ በጻፈው መጽሐፍ ላይ እንጻሰፈረው መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ የብሉይና የሐዲስ ሊቅ ናቸው፡፡ በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ብሉያትን አስተምረዋል፡፡ እንደ ጽጌ ስጦታው አጻጻፍ ከሆነ እኚህ ሰው ያላቸውን ዕውቀት በጽሑፍ አስፍረው ለቤተ ክርስቲያን ሊያበረክቱ ወደው ሳለ በጻፏቸው ጥቂት መጻሕፍት ገና ከጅምሩ "መናፍቅፀረ ማርያም" ስላሏቸው አፌን በዳቦ ብለው ትተውታል፡፡ [38]

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የክህነት ተልእኮ" በሚል ርእስ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ እመቤታችን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም "ጥንተ አብሶ" አለባት የሚል ጽሑፍ ያሰራጩበትን መጽሐፍ ከብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አባ መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ሥልጣናት ህብተ ማርያም ወርቅነህ) ጋር በጋራ አሳትመዋል፡፡ ከመጽሐፉ አንድ መቶ አምስት ገጾች ከገጽ አንድ እስከ አምሳ ሁለት ያሉትን ገጾች የጻፏቸው መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ገጾች የተጻፉት በብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አባ መልከጼዴቅ ነበረ፡፡ መጽሐፉ የተዘጋጀው በገጠርም ሆነ በከተማ ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

[38] ጽጌ ሥጦታው፣በነጋል፣፲፱፻፺፯ ዓ.ም.



ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ሲሆን ዓላማውም ኅብረተሰቡን በትምህርተ ሃይማኖትና በምግባረ ሠናይ ለማገልገል ለሚያደርጉት ጥረትና ለሥራቸው መቃናት ይረዳል ተብሎ ነው፡፡ ነገርግን ውስጡ ሲመረመር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "የውርስ ኃጢአት አለባት" የሚል ትምህርት በገጽ ፳፱ ላይ የሰፈረበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም "መንፈስ ቅዱስ አካል የለውም" የሚል ትምህርት ይዟል የሚል ተቃውሞ ቀርቦበት ነበረ፡፡[39] መጽሐፉ ከታተመ በኋላ በወቅቱ ያስተምሩበት በነበረው በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በመሰራጨቱ ነገሩ ያስቆጣቸው ተማሪዎች ጉዳዩን ለቤተ ክህነት ስላቀረቡት በጊዜው የነበረው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሊቃውንት ጉባኤ መራው፡፡ በአባቴ የሚመራው የሊቃውንት ጉባዔም መጽሐፉን ከመረመረ በኋላ በተማሪዎቹ የቀረበው ተቃውሞ አግባብነት ያለው መሆኑን ስለደረሰበት መጽሐፉ ከስርጭት እንዲቋረጥና እንዲቃጠል ወስኗል፡፡

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ቦታ በሚሰጠው በክብረ ድንግል ማርያም ላይ ይህን ሕጸጽ ያለው ትምህርት ማስተላለፋቸውን በግልጽ ባይጠቅሱትም አንድ መጽሐፍ ጽፈው አባቴ እንደተቃወማቸው፣ በዚህም ምክንያት ሳይግባቡ ቀርተው መኳረፋቸውን እንደ ገለጡለት ይብርሁ ይጥና የተባለ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲተ ተማሪ በመመረቂያ ጽሑፉ ላይ ጽፏል፡፡ [40]

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ከተማሪ ይብርሁ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ በሰጡበት ዘመን ሕጸጽ የነበረበትን መጽሐፋቸውን ያገደባቸው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ተበትኖ፣ የጉባኤው ሰብሳቢ የነበረው አባቴም ከቤተ ክህነት ታግዶ የነበረ ሲሆን የዘመኑ ሊቃውንት ጉባኤ ደግሞ ይመራ የነበረው በእሳቸው ሊቀ መንበርነት ነበር፡፡

[39] መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የክህነት ተልእኮ፣ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ፡፡

[40] ይብርሁ ይጥና፣ የመጀመሪያ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ፡፡

የአባቱ ከቤተ ክርስቲያን መሰደድ ያስደሰተው የመጋቢ ብሉይ መድፈ ተማሪና የተሀድሶ እምነት አራማጁ ጽጌ ስጦታው ይህንን ጉዳይ እንደ ተዓምር እንደሚቆጥረው በአጽንኦት ገልጿል፡፡

<u>አቶ ዓለማየሁ ሞገስ</u>

በዕድሜ ከአባቴ ብዙም የማይተናነሱት አቶ ዓለማየሁ ሞገስ የትምህርት መሠረታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን እስከ ቅኔ ድረስ መማራቸውን የሚገልጹ ታሪኮች ተመዝግበዋል፡፡ በዘመናዊ ትምህርት ረገድ በቋንቋና በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪዎችን አግኝተዋል፡፡

በርከት ላሉ ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ አስተማሪነት ሥራ ያገለገሉት አቶ ዓለማየሁ ሞገስ መጻሕፍትን በማሳተም ረገድም ተሳትፈዋል፡፡ ለየት ባለ አወዛጋቢ ባህርያቸው የሚታወቁት አቶ ዓለማየሁ ሞገስ፤ ከዚያ ባሻገር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ባፈነገጡ ንግግሮቻቸው፣ ጽሑፎቻቸውና ድርጊቶቻቸው በሰፊው ይታወቃሉ፡፡

የእመቤታችንን ቅድስና ለመልከቱም "አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ፡፡ ነገሮግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና ካሣ የማያስፈልጋት ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት፡፡"[41] በማለት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሌለ ትምሕርት ጽፈዋል፡፡ በተለያየ ጊዜ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውጪ የሆኑ ጽሑፎቻቸውን ለሊቃውንት ጉባኤ ሲያቀርቡ ይሰጣቸው የበረው ምክርና እርማት ቅር ያሰኛቸው አቶ

[41] ዓለማየሁ ሞገስ ምክብሔ ሐሳውያን በእና ቤተ ክርስቲያን።



ዓለማየሁ ሞገስ፣ በዚሁ በመጽሐፋቸው ውስጥ በአባቴ ሰብሳቢነት ይመራ የነበረው የሊቃውንት ጉባዔና አባቴንም በግል ዘልፈዋል፡፡

<u>ቄስ አስተርአየ ጽጌ</u>

ቄስ አስተርአየ ጽጌ የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ምሩቅ ሲሆኑ፣ በአሁን ጊዜ በአሜሪካን አገር ይኖራሉ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን ነኝ እያሉ እመቤታችን "ጥንተ አብሶ" አለባት ብለው የቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት ያልሆነ ትምህርትን በማሰራጨታቸው ቅሬታ ፈጥረው ቆይተዋል፡፡ አልፈው ተርፈውም ስሙን ከተሳሳተ ትምህርታቸው ጋር አቆራኝተው ስብከት መጀመራቸውን ሲሰማ አባቴ ተቃውሞ አሰምቷል፡፡

በተጨማሪም በግንቦት ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም."ዜና ልደታ" በሚል ርዕስ ያሰራጩትን ጽሑፍ በመቃወም "ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ" የተሰኘውን መጽሐፍ ጽፏል፡፡ በዚህ መጽሐፍ መቅድም ውስጥ "ቄስ አስተርአየ ስሜን ጠርተው ማታለያ አያድረጉኝ፡፡ የለኹበትም፡፡ ለራሳችኹ ታገሉ ተመለሱ እላለሁ፡፡" የሚል መልእክት አስተላልፏል፡፡ በስምንት ምእራፍ በተከፋፈለው መጽሐፍ ውስጥ አባቴ ለቄስ አስተርአየ የሰጠው መልስ በጥንተ አብሶ ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ሰጥቶባቸዋል፡፡

አባቴ በሰጣቸው መልስ ያቄሙት ቄስ አስተርአየ ጽጌ እሱ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ "የፋሲቅ ወጥመድ"በሚል ርዕስ ባሰራጩት ሃይማኖታዊ ያሁን ፖለቲካዊ (ቅጡ በማይለይ ጽሑፋቸው) አባቴ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የደከመውን ሁሉ ጥላሸት በመቀባት ብዙ ብዙ ብለዋል፡፡

በቄስ አስተርአየም ሆነ በሌሎቹም አማካይነት በአባቴ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶችን ስማንበብ ዕድሉ የገጠማቸው ምእመናን፤ ከሁሉም አቅጣጫ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በሊቃውንት ጉባዔ አባልነትና ሰብሳቢነቱ ስለቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ሥርዓት መጠበቅ ባደረገው ተጋድሎ እሱ "ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች" እያለ ከሚጠራቸው ክፍሎች

ለተለነበረበት ትችት የእሱን አመለካከት እንዲገነበቡት አስፈላጊ በመሆኑ "ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ " በሚል እዕሰ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ያሰፈረው እንደሚከተው ቀርቧል፡፡

"የፕሮቴስታንትና ልዩ ልዩ ረድፈኞች ከገቡ በኋላ ለእመቤታችን የሚሰጠው ክብር ልዕልና ቀርቶ አክብሮቱ ወደ ነቀፋ፣ ምሥጋናው ወደ ስድብ ዞሯል፡፡ የውጪ ጥገኞች ከሆኑትም ይልቅ ሰማቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ በእመቤታችን ክብር ልዕልና ቅድስና ላይ ብዙ የዓመጽ ቃል የሚናገሩና የሚጽፉ ቁጥራቸው እየጨመረ ሄዷል፡፡ ይኸውም ዲያቆናት፣ ቀሳውስት፣ ጳጳሳት እስከሚባሉት ደርሷል፡፡ በእነ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፣ በእነ ጽጌ ስጦታው፣ በእነ ቄስ አስተርአየና በጉባኤው በሌሎችም ተመሳሳይ አመለካከት በሚያራምዱ ጭምር እዝኛለሁ፡፡" [42]

<u>ቀኖናና ሥርዓትን የሚጋፋ እንቅስቃሴን መከላከል</u>
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሀዶ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት የሚጋፋ ግላዊም ሆነ ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎችን መከላከል የሲቃውንት ጉባኤው ሥራ ነበር፡፡ ይህንን በተመለከተ አባቱ ከሊቃውንት ጉባኤው አባላት ጋር በመሆንም፤ በግሉም ብዙ ሥራዎች ሠርቷል፡፡ ከጉባኤአባልነቱ፤ በተለይም በሰብሳቢነቱ እንፃር ኃላፊነቱና ግዴታዬ ነው ብሎ ያመነበትንከዳር ሳያደርስ የማፈግፈግ ጠባይ አልነበረውም፡፡ በተለይ ከራሷ ከቤተ ክርስቲያን ጉያ ወጥተው ቀኖናዋንና ሥርዓቷን ለመቀየር የተነሡትን፣ ከእግዚአብሔር ቤትነት ወደ እምባገነኖች መፈንጪያነት የለወጧትን በመቃወም፣ አቅሙ የፈቀደለትን ሁሉ ተጋድሎ ካደረገ በኋላ በመጨረሻም አውግዟቸዋል፡፡

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለዘመናት ጸንቶ በኖረባት በኢትዮጵያ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ህልውና ለመጋፋት አልፎተርፎም ለማጥፋት የተቃጡ ብዙ ሙከራዎች እንደ ነበሩ ታሪክ የሚመሰክረው ሐቅ ነው፡፡ በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ

[42] አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ዜና ሕይወት`ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ እምላክ ፡፡



እየተጠናከረ የሄደውና ከተለያዩ የሃይማኖት ክፍሎች እየተቃጣባት ያለው ተግዳሮት ክርቀት የሚሰነዘር ብቻ ሳይሆን ዓላማቸውን በላቱ በራሷ ልጆች ጭምር የሚከናወን መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች መታየት ከጀመሩ ውሎ አድሯል፡፡

ይህ ውስጣዊ የቤተ ክርስቲያን ችግር ይፋ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ አባቴ ጉዳዩን በጥንቃቄና በንቃት መከታተልጀመረ፡፡ እንዲያውም ቀደም ብሎ በዐሥራ ዘጠኝ አርባዎቹ ከቀየሳቸው የሐዋርያዊ አገልግሎት ዘርፎች በተጨማሪ እንደ ስድስተኛ የተግባር መመሪያ በማድረግ ከራሷ ከቤተ ክርስቲያን ጉያ ወጥተው ቀኖናዋንና ሥርዓቷን ለመበረዝ፣ ለመከለስና አልፎ ተርፎም ለመናድ እየሠሩ የነበሩትን እንደ አመጣጣቸው ለመመከት፤ ቤተ ክርስቲያንም በጉዳዩ ላይ ሰፊ ትኩረት እንድትሰጥ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡

አባቴ በዐሥራ ዘጠኝ መቶ ኀምሳዎቹ ውስጥ የተጀመረው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ወደ ተለያዩ የውጪ አገሮች እየላኩ የማስተማር አሠራር ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል የሚል እምነት ነበረው፡፡ ስለ ጉዳዩ እሱ የሚታየውንሥጋት ግልፅ ለማድረግ ብዙ ደክሟል፡፡ ከዚህም ጋር "ቢሆን ይሻላል" ብሎ ያመነበትን ሐሳብ በተደጋጋሚ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ኃላፊዎች ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ወደ ውጪ አገር ለሃይማኖት ትምህርት በመላክ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄና ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ጠቁሟል፡፡ በአገር ውስጥ ማስተማሩ የተሻለ ይሆናል የሚለውን አቋሙን እንደ አማራጭ ሲያቀርብ ከሚያነሣቸው ሐሳቦች ዋነኞቹ ሦስት ነበሩ፡፡ እነዚህም፣

ሀ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት፥ ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል የተረማመደች እንደ መሆኗ መጠን ለጥንታዊነቷ ቀዳሚ፥ ለእውነተኛነቷም ተገዳዳሪ እንደ ሌላት ማመንና ማሳመን የእኛ የኢትዮጵያውያን ዋነኛ ተግባር መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም እኛ ሌሎችን ማስተማር ይገባናል እንጂ ከሌሎች ሃይማኖት ለመማር መሄድ የለብንም፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መማር አለባቸው ከተባለ መማር የሚገባቸው የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ነገሮችና ዋና ዋና ዓለም

አቀፋዊ ቋንቋዎችን፥ የስብከት ዘዴ፥ የአስተዳደር ሙያዎች መሆን አለበት። እንዲህንም ደግሞ እዚሁ በአገራቸው እንዲማሩ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ይገባል።

ለ/ ሐዋርያት ገና ለስብከት ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ አስቀድሞ ሐዲስ ኪዳንን በልዩ መልእክተኛዋ አማካይነት የተቀበለችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገር በቀል እንደ መሆኗ መጠን ብሔራዊት ነች። በተደላደለው የሕገ ልቡናና የሕገ ኦሪት እርሻ ላይ ተዘርቶ የበቀለው የሕገ ወንጌል ሰብልና አገር በቀል ዕውቀት ከራሷ ልጆች ተርፎ ለሌሎችም የሚበቃ እንደ መሆኑ መጠን፤ ከብሔራዊው የክብሯ መንበር ወርዳ የሌሎችን ፍርፋሪ የምትለቃቅምበት ምክንያት የለም።

ሐ/ ወደ ውጪ አገር ለሃይማኖት ትምህርት ይላኩ ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዳንዶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በቅጡ አድቅቀው ያልዋጡ በመሆናቸው ምክንያት በሚላኩባቸው የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች አስተሳሰብና እምነት የመወሰድ ነገር ይታይባቸው ነበር። አልፎ ተርፎም ከትምህርት ሲመለሱ ውሳኔ ሰጪዎችና አስፈጻሚዎች ለመሆን በሚያስችላቸው የሥልጣን እርከን ላይ የመቀመጥ ዕድላቸው ሰፊ ነው። ይህንኑ በመጠቀም ከውጪው ትምህርት የወሰዱትን እምነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለመጫን የሚንቀሳቀሱ እንዳይሆን የሁኔታው አያያዝ መታረም ይገባዋል።

ይህ ሁኔታ አባቴን ክፉኛ ያስጨነቀውና ያሳሰበው በለ ነበረ ጉዳዩን በተለያዩ መድረኮች ላይ ያነሣው ነበር። ወደ ውጪ እየተላኩ እንዲማሩ ከተደረጉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች መካከል አንዳንዶቹ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ያራምዷቸው የነበሩ አቋሞችየአባቴን ሥጋት እውነትነት የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል። ክስተቶችን አማኝ ለማድረግ አሁን ካለንበት ዘመን የበለጠ ጊዜ አለመኖሩን በእርግጠኛነት መናገር ቢቻልም የችግሩ ፍንጮች ግን በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥትና በወታደራዊው መንግሥት ጊዜም መታየት ጀምረው ነበረ፡ ፡ ወደ ውጪ አገር ለትምህርት እየተላኩ በተመለሱ የቤተ ክርስቲያኒቱ



አገልጋዮች አማካይነት ተከስተው የነበሩ የቀኖናና ሥርዓት ጥሰቶች መካከል አባቴ በፊት ለፊት የተቃወማቸውንና የማስታውሳቸውን እንደሚከተለው ለማስፈር እሞክራለሁ።

፩ኛ/ በአንድ ወቅት ከዋነኞቹ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ የሆነውን ምስጢረ ቁርባንን ሙሉ በሙሉ የመካድ አዝማሚያ በቤተክህነቱ ውስጥ ተነስቶ ነበር። በከፍተኛ ክብር፣ ምስጢርና ጥንቃቄ ለቁርባን የሚዘጋጀውን ኅብስትና ወይን አገሪቱ ውስጥ ያሉ የወይንና የምግብ ፋብሪካዎች እያመረቱ ያቅርቡልን የሚል ጥያቄ የቀረበው በውጪ አገር ተምረው በመጡ ጳጳሳት አማካይነትነበር።

ይህን ሐሰብ ያቀረቡት የወቅቱ ልሂቃን ውጪ አገር ተምረው የመጡ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ ያቀረቡት ሐሳብ የጉባኤውን ተሳታፊዎች ፈትኖ ነበር። በዚህ ወቅት አባቴ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት መሠረት በማድረግ ባቀረበው ከፍተኛ ተቃውሞ ምክንያት ሐሳባቸውን እምክኖባቸዋል። የአባቴ አቋም አቋማቸው የሆነ ብዙዎች ሲሆኑ ያቀረበውን ሐሳብ የተቃወሙ የውጪ አገር ተማሪዎች ደግሞ ነባሩን ሥርዓት በመከነን የእነሱ አቋም ተቀባይነት እንዲያገኝ ሽንጣቸውን ገትረው ተሟግተዋል።

*"ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ኀሙስ 'ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው፤ ይህ ጽዋ ደሜ ነው' ብሎ የተናገረው እስከ ዕለተ ምጽአት የማያቋርጥ በመሆኑ ዛሬም ቄሱ ኅብስቱን በጸሎት ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ '፩ አብ ቅዱስ ፩ ወልድ ቅዱስ ፩ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ' ብሎ ሲባርከው ከኅብስትነት ወደ ሥጋ መለኮትነት፤ ከወይንነት ወደ ደመ መለኮትነት ይለወጣል።"*

በማለት ከአበው የተማረውን ትምህርተ ሃይማኖት መስክሮ ወደ ሊቃውንቱ ጉባኤ የገባው አባቴ በዚሁ መሠረት ለእምነቱ ጸንቶ በመቆሙ ቤተ ክርስቲያንንና ሕዝበ ክርስቲያንን ከከፍተኛ መሰናክልና ስብራት ጠብቋል።

ከአዕማደ ምስጢራት አንዱ የሆነው ሥርዓተ ቁርባን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በምታምነውንና በምታስተምረው መሠረት፣ የማይመረመረው ጥልቅ ምሥጢራዊና፤ መንፈሳዊ ይዘቱ ቀርቶ በሰዎች ዐቅም የሚመጠነው ዝግጅቱም እንኳ በምን ያህል አክብሮትና ጥንቃቄ እንደሚከናወን የሚያውቅ ያውቀዋል፡፡ በመሆኑም በጉባኤ በዐደባባይ ከተነሣው ሐሳብ ጀርባ ያሉት ሰዎች አንድም አላዋቂዎች ሁለትም ደፋሮች መሆናቸውን ይገነዘባል፡፡ ይህ ጉዳይ ወደ ውጪ እየተላከ በሚማሩ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ምርጫና ቅድመ ዝግጅት ላይ መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ አባቴ ገና ከጅምሩ የተሰማውን ሥጋት የሚያረጋግጥ ግዙፍ ክስተት ነበረ ለማለት ይቻላል፡፡

፪ኛ/ በውጪ አገር ተምረው በመጡ የቤተክርስቲያኒቱ የሥራ ኃላፊዎች ግፊትከተፈጸሙ ጸረ ቤተክርስቲያን ድርጊቶች አንዱ በእምነት ከማይመስሉ ጋር አብሮ የመሠለፍ ድርጊቶች ናቸው፡፡ከነዚህ ድርጊቶች አንዱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች "ብሥራተ ወንጌል" እየተባለ ይጠራ በነበረው የፕሮቴስታንቶች ሬዲዮ ጣቢያ ሰዓት ተበጥቷቸው እንዲያስተምሩ መደረጉ ነው፡፡ አባቴ ይህ በተደረገበት ወቅት በእምነት ከማይመስሉን ጋር መሰለፍ የለብንም የሚል አቋም ወስዶ ተቃውሞውን ገልጿል፡፡

ይልቁንም "ብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ" እየተባለ ይጠራ የነበረው ሬዲዮ ጣቢያ በተከፈተበት ቀን "ምድር ሆይ፥ ምድር ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ፡፡" የሚል ኃይለ ቃል ከትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ ፳፱ መጠቀሱና ለሬዲዮ ጣቢያው መከፈቻ መደረጉ የነባሪቱን ቤተ ክርስቲያንን ክብር የነካ ነው በሚል ተቃውሞታል፡፡

የሬዲዮ ጣቢያው ኃላፊዎች ያሰሙት አዋጅ ለሺ ዓመታት በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ የኖረችውን የአገራችንን፤ የሃይማኖት ቅርስና ታሪክ የካደ ሥላቅ ነው የሚል እምነት ነበረው፡፡ የቀደሙ ነገሥታት አባቶቻቸውን ሥርዓት ተከትለው ብሔራዊቷን ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ ሲገባቸው "ሃይማኖት የግል ነው፥ አገር የጋራ ነው" ሚለው መርህ በማራመድ አግባብነት የሌለው የተቀናቃኝ ብዛት በኢትዮጵያ ቤተ

ክርስቲያን ላይ ፈጥረዋል በማለትም ንጉሥ ነገሥቱን በግልጽ ወቅሷል፡፡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴዘመናዊ ነው ብለው ያመኑበትን ከላይ የተጠቀሰውን መርህ ከማራመድ አንጻር የሬዲዮ ጣቢያውን መቋቋም ቢፈቅዱም፤ ከሰዎች ፍቃድና ፍላጐት በተለየ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ላይ ልዩ ፍቃድና ፍላጐት ያለው እግዚአብሔር በዚህ የተነሳ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ እንዲያዝን ምክንያት ሆኗል የሚልአመለካከትም ነበረው፡፡

ለዚህም ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ጣቢያው ሲከፈት በሰላቅ መልክ ከቀረበው፤ "ምድር ሆይ፥ ምድር ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ፡፡" ከሚለውሐረግ ተከትሎ የተጻፈው ትንቢት በራሳቸው በዘራቸውና በዙፋናቸው ላይ መፈጸሙን በመስተዋል መገንዘብ እንደሚቻል ተናግሯል፡፡ ቃለ ትንቢቱ፤

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡፡ ከዚህ ሰው ዘር የሚከናወን በዳዊትም ዙፋን ላይ የሚቀመጥ በይሁዳም የሚነግሥ እንግዲህ አይገኝምና፡፡ መካን በመሆኑም የማይከናወንለት ሰው ብላችሁጻፉ፡፡"[43] የሚል ነው፡፡

በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ የኢትዮጵያ ቤት ክርስቲያን ሰዎች ሰብከት እንዲያቀርቡ ያደረጉት ቀድሞ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ኋላ አባ መልከ ጼዴቅ የተባሉት ሊቀ ጳጳስ ናቸው፡፡ በወቅቱ ፓትሪያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ይህንን ሐሳብ ሲቃወሟቸው ለንጉሠ ነገሥቱ የነበራቸውን ልዩ ቀረቤታ በመጠቀም ዕቅዱን ሊያስፈጽሙ ችለዋል፡፡ ለዕቅዳቸው መቃናትም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት እየተባለ ይጠራ ከነበረው ተቋም በጀት አስፈቅደው መምህራንን ይመድቡ እንደነበረ በዚሁ ሬዲዮ ጣቢያ ለስድስት ዓመታት ያስተማሩት መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ይብርሁ ይጥና ለተባለ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በሰጡት መልስ ላይ ገልጠውታል፡፡

---

[43] ትንቢተ ኤርምያስ፣ምዕ ፳፪ ፥ ፴፡፡

፫ኛ/ አባቴ "መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ" እየተባለ ይጠራ የነበረው ቤተ ክርስቲያን "የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል"ተብሎ በባዕድ ቋንቋ መጠራቱ አግባብ አይደለም በሚልም በጊዜው ቅሬታውን አሰምቷል፡፡ ከሕንጻ አሠራር ጀምሮ እስከ ስያሜአቸው ድረስ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አድባራትና ገዳማት ሃይማኖታዊ መሠረትና አገር በቀል ሥርዓት ያላቸው ስለ ሆኑ በቅርጻቸውም ሆነ በአሰያየማቸው ላይ የባዕድ አሻራ ማሳረፍ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት ነበረው፡፡ መንበረ ጸባኦት፣ ደብረ አሚን፣ ደብረ ፀሓይ፣ ደብረ ኃይል፣ ደብረ መንክራት...ወዘተ እየተባሉ የሚጠሩት አብያተ ክርስቲያን ለዚህ አማኝ ናቸው፡፡

፬ኛ/ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይካሄድ የነበረው ጸሎተ ቅዳሴ በኦርጋን መታጀቡንም አጥብቆ ተቃውሟል፡፡ የራሷ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ዜማና የምስጋና መሣሪያዎች ያሏት ቤተ ክርስቲያን ከሌላ ቦታ መዋሷ አያደምቃትም የሚል እምነት የነበረው አባቴ መንፈሳዊ ምስጢርን ከመረዳት አንጻር ኦርጋን ለእግዚአብሔር ምስጋና የተፈቀደ መሣሪያ አለመሆኑን ያምን ነበረ፡፡

ከላይ በተገለጡት ሦስት ጉዳዮች ላይ አባቴ የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት መሠረት በማድረግ ያቀረበው ተቃውሞ ለጊዜው ተቀባይ ባያገኝም በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ ይተላለፍ የነበረው ትምህርት በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ሲቋረጥ ጸሎተ ቅዳሴን በኦርጋን የማጀቡ ተግባርም እንዲቀር ተደርጓል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ወደ "ውጪ አገር ሄደው ተምረው መጡ" በተባሉ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች የተፈጸሙ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና የሚፈንገጥ መንደርደሪያ ምልክቶች ነበሩ፡፡



# ትዳርና ሥልጣነ ክህነት

የአባቴ የረጅም ጊዜ ምኞት በምንኩስና ወይም በብሕትውና ለመኖር የነበረ ቢሆንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ትዳር ሕይወት ሊገባ ችሏል፡፡ በተክለ ሃይማኖት መቃብር ቤት እየኖረ ሳለ የቤተ ክርስቲያኑ ገበዝ የነበሩ ቄስ ገበዝ ወልደ ማርያም የተባሉ ታላቅ መንፈሳዊ አባት ትዳር እንዲይዝ አዘውትረው ይመክሩት ነበረ፡፡

ከእሳቸው በተጨማሪ ደግሞ ወላጅ እናቱ ወይዘሮ አሞኘሽ ሊጠይቁት በመጡ ቁጥር በዚህ ጉዳይ ላይ አብዝተው ይመክሩትና ይወተውቱት ነበረ፡፡ እግዚአብሔር በእሱ ሕይወት ውስጥ ያለውን ዓላማ ለመገንዘብ ይረዳው ዘንድ ከቄስ ገበዝ ወልደ ማርያም ጋር ተስማምተው ሱባዔ ያዙ፡፡ የረቀቀውን ማጉላት፣ የጐደለውን መሙላት የሚቻለው አምላክ ከእግዚአብሔርም የጸሎታቸውንና የሱባዔያቸውን መልስ ሰጣቸው፡፡ ሦስት ጊዜ ደጋግመው ሱባዔ ከገቡ በኋላ ዕጣ በመጣል ያገኙት መልስ ወደ ትዳር ያደላ ሆኖ አገኙት፡፡ምንኩስናና ትዳር ተጽፎ ዕጣ ቢጣል ሦስት ጊዜም ትዳር ላይ ወደቀ፡፡ በዚህም ትዳር መያዙ የማይቀር መሆኑን አምኖ የትዳር ጓደኛ እንዲያጩለት ወደ እናቱ መልእክት ላከ፡፡ እሳቸውም በአገር ወግና ልማድ መሠረት ከዘመዶቻቸው መክረው ወይዘሮ ርብቃ ልሳነ ወርቅን አጩለት፡፡

እናቴ ወይዘሮ ርብቃ ልሳነ ወርቅ የተወለደችው የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. በቀድሞው አጠራር በጐጃም ክፍለ ሀገር በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው፡፡ እንደ አባቴ ሁሉ እናቴም በወላጆቿ በኩል ቆጥራ የምታስመሰክረው የባለአገርነት የትውልድ ሐረግ ያላት ሲሆን በአባቷ በመጋቢ ልሳነ ወርቅ ሚካኤል በኩል የጐጃም በእናቷ በወይዘሮ ዘሪቱ ከብቴ በኩል ደግሞ የጐጃምና የዳሞት ባለአባት ናት፡፡ አባቷ እሷ ሳትወለድ ቢሞቱም እናቷ ሌላ ባል ሳያገቡ በብቸኝነት አሳደጓት፡፡ በትዳር ምክንያት እንዳትለያቸው በመስጋታቸው ወደ ትምህርት ቤት አስገብተዋት ነበረ፡፡ አለቃ ንጉሤ ከተባሉ መምህር ዘንድ ፊደል ቆጥራለች፡፡ ኋላም በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለነበሩ ሕጻናት ተከፍቶ በነበረው ትምህርት ቤት ገብታ ራቅ ማሠሪያ